| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምዳዊ ፡ ጽሑፍ ፤ "ግጥም" ። |
| ርእስ ፤ | "ሰላም ፡ ለኪ ፡ ኦ ፣ ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢትዮጵያ ። " |
| ደራሲ ፤ | (አልባል) |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 11 ፡ ቀን ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2013-005 ። |
| ማስታወሻ ፤ | የድል ፡ በዓል ፡ 80 ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ግጥም

poem | poème | اشعار

ለድል ፡ በዓል ፡ 80 ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ።

## ሰላም ፡ ለኪ ፡ ኦ ፣
## ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢትዮጵያ ።

ሰላም ፡ ለኪ ፡ ኦ ፣ ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢትዮጵያ ፤
እመ ፡ አህጉር ፡ ሀገሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኬንያ ፤
ኢትዮጵያ ፡ ሀገሬ ፡ ሰላም ፡ ልበልሽ ፤
ወደ ፡ ኋላ ፡ እያሰብኩ ፡ ያ ፣ ደጉ ፡ ቀንሽ ፤
የሆሣዕና ፡ ዕለት ፡ እንዳመሰገኑ ፡ ዠግኖች ፡ ልጆችሽ ፤
ደስ ፡ ብሎሽ ፡ ብትገኝ ፡ በነጻነትሽ ፤
የተመለስሽበት ፡ ከሩቅ ፡ ስደትሽ ፤
የተባረክሽበት ፡ ከደጉ ፡ አምላክሽ ፤
ንጉሥሽ ፡ መጣልሽ ፡ መድኅን ፡ ሊኾንሽ ፤
ከተበተንሽበት ፡ የሰበሰበሽ ።
ዛሬም ፡ ይጠሩሻል ፡ እኒያ ፡ አባቶችሽ ፡ [ልጆችሽ] ፤
ድምፅሽ ፡ ቢጠፋቸው ፡ ባይታይ ፡ መልክሽ ፤
አካኼድሽ ፡ ከፍቶ ፡ ከመንገድ ፡ ወድቀሽ ፤
ተነሽ! ፡ ይሉሻል ፡ ኀይልሽን ፡ ልበሽ ፤
ዛሬ ፡ ግን ፡ ልንገርሽ ፥ ግብርሽ ፡ ተለውጧል ፤
አንቺው ፡ ዕርሻ ፡ ኹነሽ ፡ አንቺው ፡ ዘር ፡ ኹነሻል ፤
ዐራሾች ፡ በጃቸው ፡ ይበታትኑሻል ።
የሰማይ ፡ ሰራዊት ፡ ዘንዶውን ፡ ተዋጉት ፤
ጥሶ ፡ የመጣውን ፡ የድንበር ፡ መሠረት ፤
የሮማ ፡ ግብረ ፡ ኀይል ፡ ያ ፡ መርዘኛው ፡ ዘንዶ ፤
ከባሕር ፡ ላይ ፡ ወድቋል ፡ ቾብቾቦውን ፡ ታርዶ ።
አይተናት ፡ ነበረ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ረክሳ ፤
ያምስት ፡ ዓመት ፡ ስደት ፡ ኾኖባት ፡ አበሳ ፤
ግፍ ፡ አይቀርምና ፡ ጠላቷን ፡ ደምስሳ ፤
እንደገና ፡ አየናት ፡ ዙራ ፡ ተመልሳ ፤
በኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዳግም ፡ ተቀድሳ ።
ትንሽ ፡ ተመገቢ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሀገሬ ፤
እየረገፈ ፡ ነው ፡ የዛፎቹ ፡ ፍሬ ፤
የዘላለም ፡ ቤቴ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነሽ ፧
በኖራ ፡ ተሠርተሽ ፡ እንዴት ፡ ትፈርሻለሽ ፧
እውነት ፡ ኖራ ፡ ቢኾን ፡ የተሠራሽበት ፥
አትፈርሽም ፡ ነበረ ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ዘበት ።
እኔ ፡ ምን ፡ እላለኹ ፥
ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ እናገራለኹ ፤
የጥንቱን ፡ ወራሪ ፡ መውደቁን ፡ እያሰብኩ ፤
ዛሬ ፡ ተመልሼ ፡ (ኢትዮጵያን) ፡ ብፈልግ ፡ ዐጣኋት ፤
ከሰው ፡ ተሰውራ ፡ ጠፍታ ፡ አገኘኋት ፤
ጠባይዋ ፡ አስቸገረኝ ፡ የሚል ፡ ድ̇ር̇ስ ፡ ም̇ል̇ስ ፤
በጣም ፡ ያሳዝናል ፡ ወይ ፡ ተሠርቶ ፡ መፍረስ ።

ዘተአረየ ፤ ሚያዝያ ፡ 11 ፡ ቀን ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ፥
ኢትዮጵያ ፨


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።